የሚከተሉት ታሪኮች ከኢየሱስ ምሳሌዎች የተጠቀሱ ናቸው። አንዳንድ ታላቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላት ለየት ያሉ ናቸው። ትምህርቱ ግን በእውነት የኢየሱስ ትምህርት ነው።

ማቴ. 7፡15—20
ማቴ. 13፡31—32
ማቴ. 13፡33
ማቴ. 13፡44
ማቴ. 13፡45—46
ማቴ. 13፡47—50

ኢየሱስ አስተማረ ፡—

ከሐሰተኛ ነቢዮች ተጠንቀቁ ።

ሐሰተኛ ነቢዮች ወደ እናንተ ሲመጡ እውነተኛ
ክርስቲያኖችን ይመስላሉ ።
በሥራ ግን አረመኔዎች ናቸው ።

በሥራቸውና በንግግራቸው እነርሱን ታውቃላችሁ ።

ሰው ቡና ተክሎ እሾህ ይለቅማልን ?



ወይስ ስንዴ ዘርቶ እንክርዳድ ያጭዳልን ?

ንጹሕ ምንጭ ጥሩ ውኃ ይሰጣል ።

ከመጥፎ ጉድጓድ መራራ ውኃ ይገኛል ።

ንጹሕ ምንጭ መራራ ውኃ አይሰጥም ።

ከመጥፎ ጉድጓድ ጥሩ ውኃ አይገኝም ።

አንድ ምንጭ ጥሩ ውኃ ባይሰጥ ማንም አይፈልገውም ።

ሐሰተኛ ነቢዮች እንደ መራራ ውኃ ናቸው ።

የእነርሱን ትምህርት ስትቀምሱት ታውቁታላችሁ ።

ግን መራራውን ትምህርት ከመቅመስ መጠንቀቅ ይሻላል ።



ኢየሱስ እንዲህ አለ፡—

አዋቂ ማን ነው?

የእኔን ቃል የሚሰማና የሚፈጽመው እርሱ አዋቂ ነው።

አዋቂ ሰው ቤቱን ሲሠራ ደህና ጉድጓድ ይቆፍራል።

ግድግዳውን ያቆማል።

ነፋስ ይነፍሳል፤ ዝናብ ይዘንባል፤ ጐርፍ ይጐርፋል።

ምንም ቢመጣ ቤቱ አይወድቅም ግድግዳው የጠነከረ ነውና።



ሞኙ ማን ነው ?

እርሱ የእኔን ቃል ይሰማል ፣

ነገር ግን አይታዘዝም ።

ደህና አድርጐ ሳይቆፍር ግድግዳውን ቶሎ ብሎ አቆመው ።

ነፋስ ነፈሰ ፣ ዝናብ ዘነበ ፣ ጐርፍ ጐረፈ ፣ ቤቱም ወደቀ ።

ለምንም አይጠቅምም ።



አይሁዶች ስለ ኢየሱስ እንዲህ አሉ፡—
ይህ ሰው መልካም ሥራ የሚሠራ በሰይጣን ኃይል ነው።
ኢየሱስ ግን ሃሳባቸውን አወቀ እንዲህም አለ፡—
የአንድ አገር ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ ያ አገር ብላሽ ነው።
የአንድ ከተማ ወይም የአንድ ቤት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ ከተማው ወይም ያ ቤት
ጠላትን ለመከላከል አይችልም።



ሰይጣን የራሱን ሥራ ቢያፈርስ ከራሱ ጋር ተጣላ ማለት ነው።

ከራሱ ጋር ከተጣላ ሌላ ሥራ ለመሥራት ምን ኃይል አለው?

እኔ በሰይጣን ኃይል ብሠራ የእናንተ ልጆች በማን ኃይል ይሠራሉ? እስቲ ንገሩኝ? ፍረዱ።

አንተ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ትሠራለህ ብትሉኝ የእግዚአብሔር ኃይል በመካከላችሁ አለ ማለት ነው።



ዛፉ ጥሩ ነው ብትሉ ፍሬው ደግሞ ጥሩ ነው በሉ ።
የዛፉ ፍሬ መጥፎ ነው ብትሉ እንግዲህ ዛፉ መጥፎ ነው በሉ ።
የዛፉ ዓይነት ከፍሬው ይታወቃል ።
እናንተ ጠማማ ሰዎች ልባችሁ ጠማማ ሲሆን መልካም ነገር እንዴት ትናገራላችሁ?
የሰው ንግግሩ ከልቡ ነው ።



መልካም ሰው ከንጹሕ ልቡ ደኅና ነገር ይናገራል ።

መጥፎ ሰው ግን ከጠማማ ልቡ መጥፎ ነገር ያወጣል ።

ስሙ ፡—

ሰው ያለጥንቃቄ ብዙ ይናገራል ።

በፍርድ ቀን ለንግግሩ ሁሉ ፍርድ ይቀበላል ።

የሰው ንግግር የልቡን ዓይነት ያሳያል ።

ስለዚህ ፍርዱ እንደ ንግግሩ ይሆናል ።

መጥፎ ሰው ጠማማ ነገርን ይናገራል ።

ስለዚህ ፍርዱ እንደ ንግግሩ ይሆናል አለ ኢየሱስ ።



ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦—

አንድ ገበሬ ስንዴ ለመዝራት ተነሣ ።

ጥቂት ስንዴም በመንገድ ላይ ወደቀ ፤

ወፎችም በሉት ።

ሌላው ስንዴ በድንጋያማ ቦታ ወደቀ ፤

ሁሉም ደርቆ ጠፋ ፤

ምንም ሥር አልነበረውም ።



ጥቂት ስንዴ በእሾህ መካከል ወደቀ ።

ያ ቦታ ስላልታረሰ ስንዴው አላደገም ።

ሌላው ስንዴ በመልካም መሬት ስለወደቀ

ሁሉም ፍሬ ሰጠ ።

ባንዳንድ ቦታ ትንሽ ፍሬ ሲሰጥ ባንዳንድ ቦታ ፍሬው

ብዙ ነበር ።

ከሌላ ቦታ ግን እጅግ ብዙ ፍሬ ተገኘ ።

መንፈሳዊ ትምህርት ብትፈልጉ ይህንን ምሳሌ አስቡ ።

በመሬት ምሳሌ ሰማችሁ ።

አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ

አይገባቸውም ።



ሰይጣን እንደ ወፍ መጥቶ ያንን ቃል ለቅሞ ይወስዳል ።

በመንገድ ላይ የወደቀው የዚያ ስንዴ ትርጉም ነው ።

በድንጋይ ላይ የወደቀው ስንዴ ትርጉም እንዲህ ነው ።

አንዳንድ ሰዎች ቃሉን ሲሰሙ እሺ ይላሉ ፤ ለጊዜው ብቻ ይደሰታሉ ።

ስለሃይማኖት ፈተናና ስድብ ሲቀበሉ ግን በድንጋይ ላይ እንደወደቀው ስንዴ ይደርቃሉ ።



በእሾህ መካከል የወደቀው ስንዴ እንዲህ ነው ።

ቃሉን ሲሰማ እሺ ይላል ።

እርሱ ግን ሐሳቡ ሁሉ ስለ አሁኑ ዓለም ነው ።

ገና ከዚህ ዓለም ብዙ ሀብት ይፈልጋል ።

ስለዚህ በሕይወቱ ምንም መንፈሳዊ ፍሬ አይታይም ።

አንዳንዶች ወንጌልን ሲሰሙ ይገባቸዋል ።

እነርሱ በመልካም መሬት እንደወደቀው ስንዴ ናቸው ።

ብዙ ፍሬ ይሰጣሉ ።

ከአንዳንዱ ትንሽ ፍሬ ይገኛል ።

ሌላው ብዙ ፍሬ ይሰጣል ።

እጅግ ብዙ ፍሬ የሚሰጥም አለ ።



ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦—

የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲህ ነው ፦አንድ ሰው በእርሻው መልካም ስንዴ ዘራ ። ግን የሰውየው ጠላቶች መጥተው በስንዴው መካከል አንድ ሌላ ዘር ዘሩ ።

ዘሩም ባደገ ጊዜ መልኩ እንደ ስንዴ ነበር ።

ነገር ግን ለምንም አልጠቀመም ።



አበባ ባወጣ ጊዜ ልዩነቱ ታወቀ።
የሰውየው ሠራተኞች መጡና እንዲህ አሉት ፦—
አንተ ደህና ስንዴ ዘርተህ ይህ የማይረባ
ስንዴ መሳይ ከየት መጣ ?
ሰውየውም አላቸው ፦—
ይህንን አንድ ጠላት አደረገው።
ሠራተኞቹ እንዲህ ብለው ጠየቁት እንሂድ
ይህንን ስንዴ መሳይ እንንቀል አሉት።
ሰውየው ግን እንዲህ አላቸው ፦—



አይሆንም እሱን ስትነቅሉ ምናልባት ብዙ ስንዴ
ትነቅላላችሁ።

ለጊዜው ሁለቱም ይደጉ።

ሰዎች እህሉን ለመሰብሰብ ሲወጡ ትእዛዝ
እሰጣለሁ።

በመጀመሪያ ጣላቱ የዘራውን ሰብስቡና ባንድ
ቦታ አስቀምጡ በኋላ በእሳት እናቃጥላለን።

በኋላ ደህናውን ስንዴ ወደ እኔ አምጡ እላለሁ።

ይህን ከተናገረ በኋላ የኢየሱስ ተማሪዎች
እንዲህ አሉት፡—



የዚህ ምሳሌ ትርጉም ምንድር ነው?

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፦—

ይህንን መልካም ስንዴ የዘራው ሰውየው እኔ ነኝ ።

እርሻው የዓለም ምሳሌ ነው ።

የመልካሙ ስንዴ ምሳሌ ክርስትያኖች ናቸው ።

ጣላቱ የዘራው ስንዴ መሳይ ዘር የሰይጣን

ልጅ ምሳሌ ነው ።

የመሰብሰቢያው ጊዜም በዓለም መጨረሻ ነው ።

በዚያን ጊዜ መልእክተኞቼን እልካለሁ ።



በኃጢአት የሚደሰቱትንና ሕጌን
የማይጠብቁትን ከእውነተኛ ክርስቲያኖች
መካከል ይሰበሰባሉ ።
ለምንም የማይጠቅሙ ስለሆኑ ወደ ቆሻሻ ጉድጓድ
ይጥሉአቸዋል ።
በዚያ የማይጠፋ እሳት አለ። ለምህረት ይጮኸሉ ፤
በሕመም ምክንያት ጥርሳቸውን ያፋጫሉ ።
የእውነተኛ ክርስቲያኖች ሽልማት እንደ ፀሐይ
ስለሚያበራ በሥጋዊ ዓይን አይታይም ።
የእግዚአብሔርን ክብር ይካፈላሉ ።
መንፈሳዊ ትምህርት ብትፈልጉ ይህንን ምሳሌ አስቡ ።



ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው ፦—

በዚህ ዓለም የእኔ ቤተ ክርስቲያን የባሕር ዛፍ ዘርን ትመስላለች ።

ሰው መስዶ በወንዝ ዳር ዘራው ።

ከዘር ሁሉ በጣም ትንሹ ነው ።

ከሃያ ዓመት በኋላ ግን እጅግ ትልቅ ዛፍ ሆነ ።

ከትልቅነቱ የተነሣ ልዩ ልዩ ዓይነት ወፎች በዚያ ለማደር ይችላሉ ።



በሌላ ምሳሌ ኢየሱስ እንዲህ አለ፦—
ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ስኳር ናት።
አንድ ሰው በሻይ ጨመራት።
ያ ሻይ ጣፋጭ ለመሆን ቻለ።



ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦—

ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን በወንዝ

እንደ ተገኘች ወርቅ ናት።

አንድ ሰው ወርቅ አገኘና ለማንም አልነገረም።

ከብቱንና ሌላ መሬቱን ሁሉ ሸጠ።

በወንዙ አጠገብ ያለውን መሬት ሁሉ ገዛ።



ስለ ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ እንዲህ አለ፦—

አንድ ሰው ቆንጆ ቆንጆ ቤት ስለ ፈለገ ብዙ
ቤቶች ገዛ።

አንድ ቀን የፈለገውን ዓይነት ቤት አገኘ ነገር ግን
በጣም ውድ ነበር።

ገንዘቡም አልበቃውም።

የገዛቸውን ቤቶች ሁሉ ሸጠና ያን ዓይነተኛ
ቤት ገዛ።



ኢየሱስ በምሳሌ እንዲህ አለ፡—

ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ተማሪ ሱሪ
ኪስ ናት።
በቀን ውስጥ ብዙ ነገር ይሰበስባል።
ሲመሽ ከኪሱ ያለውን አውጥቶ ቆሻሻውን ይጥላል።
ጥሩ ነገርን ሁሉ በደህና ቦታ ያስቀምጣል።
በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል።
የሰማይ መላእክት ይመጣሉ።



ከእውነተኛ ክርስቲያኖች መካከል ሌሎችን
ይሰበስባሉ ።
ልጁ ከኪሱ ያለውን ቆሻሻ እንደ ጣለ እንዲሁ
እነዚያ ወደ ቆሻሻ ጉድጓድ ይጣላሉ ።
ለምሕረት ይጮኻሉ ።
በሕመም ብዛት ጥርሳቸውን ያፋጫሉ ።



ምን ታስባላችሁ?

አንድ ሰው መቶ በግ ነበረው በመሸ ጊዜ

ዘጠና ዘጠኝ ብቻ ተገኙ። ነገር ግን

እነዚህ ዘጠና ዘጠኝ በጎች ደህና ቢሆኑም

የጠፋውን ለመፈለግ አይሄድም ወይ?

የጠፋውን በግ ሲያገኝ ምን ያደርጋል?

በጣም ይደሰታል።

ሌላ ዘጠና ዘጠኝ አለው። ነገር ግን

አልጠፉም ስለዚህ ለጊዜው ስለነርሱ አይደሰትም።

የጠፋውን ስላገኘ ግን በጣም ተደሰተ። ታላቅ

እረኛችን አምላካችን ነው።

ከአሕዛብ አንድ ትንሽ ልጅ እንኳ እንዲጠፋ

ኢየሱስ አይፈልግም።



ስለ ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ አንድ
ሌላ ምሳሌ ተናገረ እንዲህ ሲል፥
አንድ ቀን የሠራተኞቹን ደመወዝ ለመክፈል
ሠራተኞቹን ሁሉ ሰበሰበ። ከሠራተኞቹ አንዱም
የአሥር ሺህ ብር ዕዳ ነበረበት።
ዕዳውን ለመክፈል አንድ ቀይ ሳንቲም
አልነበረውም።
ጌታው እንዲህ አለው።
ዕዳህን እንድትከፍል አንተንና ሚስትህን፥
ልጆችህንም ያለህንም ሁሉ እሸጣለሁ።
ያ ሠረተኛ ግን በጌታው እግር ወድቆ
እንዲህ አለው፥



ማረኝ፤ ማረኝ ሁሉን ለመክፈል እሞክራለሁ ።
በዚህን ጊዜ የጌታው ልብ ተነካና ይቅር አለው ።
ባሰላም ወደቤትህ ተመለስ አለው ።



ከጌታው ዘንድ እንደወጣ ያ ሠረተኛ ከጓደኞቹ
አንዱን አገኘው ።
ጉሮሮውን ይዞ እንዲህ አለው፣
ከኔ የተበደርከውን አሥር ሳንቲም አውጣ
ክፈለኝ ። በዚህን ጊዜ ተዳበሪው ምሕረት ለመነ ።
እባክህ ታገስ ነገ እሰጥሃለው አለው ።



እንቢ ብሎ ያንን አሥር ሳንቲም እስኪከፍል
ድረስ በሠራተኞቹ ኃላፊ ዘንድ አሳሰረው።
ሌሎች ሠራተኞች ይህንን ሲያዩ በጣም አዘኑ።
ወደ ጌታቸው ሄደው ሁሉን ነገሩት።
የሠራተኞች ጌታ ያን ጨካኙን ሠራተኛ ጠርቶ
እንዲህ አለው፡
አንተ መጥፎ ሰው በለመንኸኝ ጊዜ ያንተን ዕዳ
ሁሉ ተውኩ።



ለአንተ ምሕረት እንዳደረግኹኝ ለጓደኛህ
ምሕረት ማድረግ አይገባህም ነበር።
የሠራተኞች ጌታ በጣም ተናዳደ።
ያን ጠማማ ሠረተኛ የመጨረሻውን ሳንቲም
እስኪከፍል ድረስ በኃይል ቀጣው።
የናንተ ልብ ካልተለወጠና ከእግዚአብሔር አዲስ
ልብ ካልተቀበላችሁ ምሕረት ለማድረግ
አትችሉም።
በእውነት ምሕረት ለማድረግ ባትችሉ
እግዚአብሔር ለእናንተ ምሕረት አያደርግም።



ኢየሱስ እንዲህ ሲል አንድ ሌላ ምሳሌ ተናገረ ፦-
አንድ ሰው መሬት ገዛ ደህና አጥር አቆመ ።
ቦታውን አርሶ ስንዴ ዘራ ፣
ጐተራ ገዛ ለሠራተኞች አስረክቦ ወደ አገር ቤት
ሔደ ።

ስንዴው በደረሰ ጊዜ ከአገር ቤት አሽከሮች ላከ ።
ሒዱ እህሌን ጭናችሁ አምጡልኝ አላቸው ።
ሠራተኞቹ ግን ከአሽከሮች አንዳንዱን ደበደቡ
አንዳንዱን በድንጋይ ወገሩና አንዳንዱን
ገደሉ ።

ሰውዬው እንዲሁ ሌላ አሽከሮች ላከ ።



ሠራተኞቹ እንዲሁ እያደረጉ እነሱንም አባረሩ።
ከሁሉ በኋላ ሰውዬው እንዲህ አለ፦
ልጄን አይነኩም እርሱን እልካለሁ።
ሠራተኞች ግን ልጁን አዩና እንዲህ አሉ፦
እሰይ ይህ ወራሹ ነው፤
ብንገድለው መሬቱ የኛ ይሆናል።
የሰውዬውን ልጅ ገደሉ ባለመሬቱ ሲመጣ
በእነዚህ ሠራተኞች ላይ ምን ያደርጋል?
አይሁዶች ለኢየሱስ ሲመልሱ እንዲህ አሉት፦
ባለመሬት ሲመጣ እነዚህን መጥፎ ሠራተኞች ይገድላል።
መሬቱን ለታማኝ ሠራተኞች ይሰጣልና።



ኢየሱስ ሲያስተምር እንዲህ አለ፦
ይህንን እወቁ።
ሌባ መቼ እንደሚመጣ ማን ያውቃል?
ባለቤቱ ቢያውቅ ኑሮ ሳያንቀላፋ ንብረቱን
ይጠብቅ ነበር።
ሌባውንም ይከላከል ነበር።
የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን ስለማታውቁ
ተጠበቁ።



ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
ኀ	ኁ	ኂ	ኃ	ኄ	ኅ	ኆ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ

የ	ዩ	ዪ		ዬ	ይ	ዮ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
ጰ	ጱ	ጲ	ጳ	ጴ	ጵ	ጶ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ

ሏ	ሟ	ሯ	ሷ	ቧ	ቧ	ቷ
ቿ	ኗ	ኟ	ዟ	ዧ	ዷ	ጧ
		ዏ	ጷ	ፏ		

ኰ	ኵ	ኳ	ኴ	ዀ
ጐ	ጕ	ጓ	ጔ	ጒ
ቈ	ቍ	ቋ	ቌ	ቊ
ጐ	ጕ	ኋ	ኌ	ጎ